| | |
|---|---|
| ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ<br>ኢየሱስ ክርስቶስ<br>ካህኑ ለዓለም፡ በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ<br><u>ንጉሠ ጽዮን፥ ወንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ</u> | ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር<br>ድንግል ማርያም<br>እሙ ለአምላክነ፥ ወእምነ ዘዚአነ<br><u>ንግሥተ ጽዮን፥ ወንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ</u> |
| The Conquering Lion of the Tribe of Judah<br>Jesus Christ<br>Eternal Priest in the Order of Melche-Zedeq the Ethiopian<br>King of Zion and King of Kings of Ethiopia | Ethiopia stretches out Her Hands to God<br>The Virgin Mary<br>Mother of God and Our Holy Mother<br>Queen of Zion and Ethiopia |

ቍጥር ፬/፳፻፰ ዓ. ም.

# ቃለ ዐዋዲ!

## እምኢትዮጵያ፡ ዘመንግሥተ እግዚአብሔር።

# የአዋጅ ቃል!

## ከኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት።

በስመ እግዚአብሔር አብ፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ፤
አሓዱ አምላክ፤ በቅድስት ሥላሴ፤
በስመ እግዝእትነ፥ ወእምነ፥ ወሃይማኖትነ፥ ወሀገሪትነ፥ ወንግሥትነ፡
ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ፤
በኃይለ መስቀሉ፡ ዘእግዚእነ፥ ወአቡነ፥ ወመድኃኒነ፥ ወካህንነ፥ ወንጉሥነ
ኢየሱስ ክርስቶስ፡
ወልደ-እግዚአብሔር ሕያው፥ ወወልደ ማርያም ሥግው።

\+ \+ \+

# ይድረስ፡-

## ለኪዳናውያንና ለኪዳናውያት
## የቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያ ልጆች!

### ስለሰላምታ አሰጣጣችን ሥርዓት፡
### የተሰጠ ማብራሪያ።

ኪዳናውያንና ኪዳናውያት የኾኑት የቀደሙት ወላጆቻችን፡ "እጃችሁን ለማንም አትስጡ! አትማረኩ!" ብለው በማስጠንቀቅ፡ "እጅ ንሡ!" ያሉበትን፡ የቅዱሱን ኪዳን የሰላምታ አሰጣጣችንን ሥርዓት፡ ኹላችንም የምናውቀው ነው።

ይኹን እንጂ፡ በአኹኑ ጊዜ፡ እርስ በርሳችንም ኾነ፡ በተለያዩ የዓለም ኅብረተ ሰቦች መካከል በምንኖር፡ በዛሬዎቹ ታማኞች ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቻቸው ዘንድ፡ ይህንኑ ሥርዓታችንን፡ በተግባር ላይ የማዋሉ ዓቅም፡ ሊከብድ እንደቻለ፡ ይኸው፡ እየደረሰ ባለው አስቸጋሪ ኹኔታ ይታወቃል።

ስለዚህ፡ ይህን የማያስፈልግ ችግር ለማስወገድ፡ ከዚህ የሚከተሉትን እውነታዎች ተከትሎ መፈጸሙ፡ ተገቢና ጠቃሚ በመኾኑ፡ ስለሰላምታ አሰጣጣችን ሥርዓት፡ ይህን ማብራሪያ፡ በቃለ ዐዋዲ፡ ይፋ ማውጣቱ፡ አስፈላጊ ኾኗል።

፩ኛ፡ "እጅ ንሡ!" ማለት፡ እንደመማረክ የሚያስቈጥረውን፡ "እጃችሁን፡ ለሰላምታም ቢኾን፡ አስቀድማችሁ ዘርግታችሁ፡ ለሌላ አትስጡ!" ማለት እንጂ፡ "ሌላው፡ በራሱ ፈቃደኛነት፡ እጁን፡ ለወዳጅነት ሰላምታ፡ አስቀድሞ ዘርግቶ ቢሰጣችሁ፡ አትጨብጡት!" ማለት አለመኾኑን ተረድተን፡ በዚሁ መሠረት መፈጸሙ፡ አግባብ ይኾናል።

፪ኛ፡ "እጅ ንሡ!" ማለት፡ ቀጥተኛ መልእክቱ፡ ከላይ እንደተገለጸው፡ "በምንም፥ ወይም፡ ለምንም ምክንያት፡ እጃችሁን አትስጡ!" ማለት እንጂ፡ ለሰው ወደመስገድ ፈለግ እያዘነበለ የሚኼድ፡ የአምልኮት መንገድን እንደመከተል የሚያስቈጥረውን፡ "ከአንገታችሁ፥ ወይም፡ ከወገባችሁ ጭምር፥ ወይም፡ በሙሉ አካላችሁ አጐንብሱ!" ማለት አይደለም። ስለዚህ፡ "እጅ አነሣሥ" የሚባለው ሥርዓት፡ በአፈጻጸሙ በኩል የሚታይበት ድርጊት፡ ከሃይማኖታዊዉም ኾነ ከምግባራዊው መመሪያ ጋር ያልተያያዘና ያልሠመረ ኾኖ ይገኛል።

ይህንም እውነታ፡ መልአኩ፡ ለባለራእዩ ዮሓንስ፡ "ኢትስግድ ሊተ! ዑቅ! ዮጊ፡ እስመ አነ ገብር ዘከማከ፥ ወዘአኀዊከ ነቢያት፥ ወዘእለ የዐቅቡ፡ ቃለ ዝንቱ መጽሓፍ። አንተሰ፡ ለእግዚአብሔር ስግድ!" ማለትም፡ "ዕወቅ! ተጠንቀቅ! ለእኔ አትስገድ! እኔም፡ እንዳንተና እንደወንድሞችህ ነቢያት፥ የዚህን መጽሓፍ ቃል እንደሚጠብቁም ካህናት፡ አገልጋይ ነኝ። አንተስ፡ ለእግዚአብሔር ስገድ!" ብሎ የነገረው ቃል፡ ፈጽሞ ግልጽ ያደርገዋል። (ራእ. ፳፪፥ ፱።)

በዚህ መሠረት፡ የእኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ የሰላምታ አሰጣጡ ሥርዓት፡ <u>በእኩልነት ደረጃ</u> የሚፈጸመው፡ እንደሚከተለው መኾኑ፡ ሊታወቅ ይገባል፡-

በሩቅ ሲኮን፡ በድምፅ በሚሰሰማና በንግግር በሚለዋወጡት፡ የእግዚአብሔር ሰላምታ ይካኼዳል።

በቅርብ ሲኮን ደግሞ፡ በኹለቱ ወገኖች መካከል እንዳለው፡ እንደእውቀቱ ቅርበትና እንደፍቅሩ መጠን፥ እንደዕድሜውም መበላለጥ፡ ተቃቅፎ ወይም፡ እጅ ለእጅ ተያይዞ፡ ትከሻ ለትከሻ፥ ወይም፡ ጉንጭ ለጉንጭ፥ ወይም፡ እጅ ለእጅ በመሳሳም ይከናወናል።

ይህም፡ "ተአምኁ በበይናቲክሙ፤ በአምኃ ቅድሳት!" ማለትም፡ "በተቀደሰች አሳሳም፡ እርስ በርሳችሁ፡ 'ሰላም!' ተባባሉ! ሰላምታን ተሰጣጡ!" በሚለው፡ በሓዋርያው ቃል ጸንቶ፡ ሲሠራበት የቀጠለ መኾኑ ይታያል። (፩ቆሮ. ፲፮፥ ፳፤ ፪ቆሮ. ፲፫፥ ፲፪።)

\+ \+ \+

*ተዐውደ፡ በኅዳር ፳፯ ቀን፥ ፳፻፯ ዓመተ ምሕረት፡ ታወጀ።*

ላእከ ኢትዮጵያ፡ ዘመንግሥተ እግዚአብሔር፣
የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ አገልጋይ፣
ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ፤
ስመ ጥምቀቱ፡ ኂሩተ-ወልድ።